**ክፍል ሁለት**

# አራተኛውን አገርአቀፋዊ ምርጫ እኛን በሚጠቅም መንገድ ስለማከናወን

*(በምንኖርበት አለም ይህን ማን ያጣዋል የሚባል ነገር የለም የአሜሪካ ፕሬዘዳንት ወቶ አሁን የተነሳውን ስዋዬን ይተሰኘውን ወረርሽኝ ለመከላከል እጃችሁን ታጠቡ; ስታስሉ በመሀረብ አፋችሁን ሸፍኑ.... ለኛም እንደዚህ አይነት ጉዳዮች ሊገቡን ይገባል)*

በክፍል አንድ ጽሁፋችን ዛሬ ውሳኔ ያስፈልገዋል በአልነው አራተኛውን አገራቀፋዊ ምርጫ በሰላም ለመታገል ምርጫ ያደረጉ ተቃዋሚዎች ቢካፈሉ ይሻላል ወይስ በአይካፈሉ?። አንካፈልም ብለው አቋም ወስደው ወይም ተካፍለው የተሳካ ውጤት ማምጣት ከአልቻሉ የመጨረሻ ውጤቱ ከሁለቱም አማራጭ ወያኔ ተጠቃሚ ሆኖ እንዴት እንደሚወጣ ፍራቻችንን ለማሳየት ሞክረናል። በዚሁ ጽሁፋችን ልናሳይ እንደሞከርነው በሰላማዊ መንገድ ለመታገል ለመረጡት አይመርጡትም እንጂ አንካፈልም የሚለው ቀላሉ አማራጭ መሆኑን ነው። ምን አልባት ምርጫ ከአደረጉት ግን ቀላል ምርጫ ስለሆነም የሚያመጣውም ውጤት እዚህ ግባ የማይባል እንደውም ጎጂም ሊሆን ይችላል። እውነተኞቹ ተቃዋሚዎች በአይካፈሉም የሚካፈሉ መኖራቸው አይቀርም። ድምጽ በአያገኙም ተተምኖ ይሰረቅላቸዋል። በሌላ በኩል ተካፈልንም ይለበቂ ዝግጅት በቀላሉ ኮሮጆ እንዲገለብጥ እድል ሰተነው መወዳደር የለብንም። ሁለቱም ወያኔን ስልጣኑ ላይ ከአሁኑ በተሻለ ምክንያታዊ ሆኖ እንዲቀጥል ያደርጉታል። ችግሮች አሉ በደንብ ነገር ገን ዛሬ አሉ የምንላቸው ችግሮች እስካልተጋፈጥናቸው ነገም ተጠናክረው ይኖራሉ። አንካፈልም የሚለው ውሳኔ በይበልጥ አገርቤት የሚደረገውን  ትግል የሚጎዳ ሲሆን የትኛውንም አይነት ትግልም ተጠቃሚ አያደርገውም። ለሁሉም ትግል አጋዥ የሆነውን ሰላማዊውን አገር ቤት የሚደረገውን ትግል ሊያጫጫው ህዝብም ዘንድ መሰረት ሊያሳጣው ይችላል።

የቀረው ምርጫ ተቃዋሚዎች ምርጫው ላይ መካፈል አለባቸው ምርጫውን በዛም ብለን በዚህ እኛን አሸናፊ በሚያድረግን፤ ለትግሉ የሚጠቅመንን ነገሮች በምናወጣበት መንገድ መከወን አለብን የሚለው  ነው። ይህ ደግሞ ምርጫ ለማካሄድ ምንም የተመቻቸ ነገር በሌለበት ችግሮቹን መሰናክሎቹን እንዴት አልፈን ነው  የተሳካ ተብሎ የሚቆጠር ውጤት ማስቆጠር የምንችለው? ውጤታችንንስ ከቀማኛ መጠበቅ የምንችለው? የሚል መልስ የሚሻ ጥያቄ ያስነሳል። ችግሮቹ አንድ ሁለት ተብለው ተቆጥረው ብዙ ናቸው። መብዛታቸው ብቻ ሳይሆን መፍትሔያቸው  ከባባድ ነው። በመጀመርያ ትግል ላይ ነን በዚህ አለም ላይ ችግር በሌለበት በተመቻቸ ሁኔታ ውስጥ የሚደረግ ትግል የለም። ስለዚህም ችግሮች ለምን ኖሩ ማለት አንችልም። ችግሮቹን መጋፈጥ የግድ ነው። ያለው ምርጫ መፍትሄ መፈለግ፤ ለመቋቋም መዘጋጀት፤ ማቅለያ መንገድ ከአለው ማሰብ ነው። ትርፍና ኪሳራው በኛ ማሰብ ማቀድ መተግበር ላይ ነው የሚወሰነው።

ጥሩው ነገር አሉ ያልናቸው ችግሮች ላይ መፍትሄ ለማሰቢያም ለማቀድ ለመዘጋጀት ረጅም ጊዜም በአይሆን ከበፊቱ ምርጫ የተሻለ ጊዜ አለን። ዛሬ ከጀመርን ማለታችን ነው። አገር ቤት እየተንቀሳቀሱ ያሉት ፓርቲዎች እያደረጉ

ከአሉት እንቅስቃሴ፣ ከቀረው ጊዜ አኳያ ስናየው ምርጫው ላይ ከገቡ የሚቀጥለውም ምርጫ ግርግር የበዛበት የዘመቻ እንደሚሆን መጠበቅ ቀላል ነው። በትግል ምርጫ ደረጃ ሁለገብ ቢሉም አገር ቤት ስለሚደረገው ሰላማዊ ትግል ፍላጎቱ እያነሰ የመጣውም ህዝብ፣ እያመነበት ድጋፍ የማይሰጠውም፣ በአንድኛውም የሚቃወማቸውም በእለቱ መጨረሻ ውጤት መጠበቁም አይቀርም። መጠበቅ ብቻ አይደለም ውጤትን ይጠይቃል። ተአምር አይሰሩ። ሳይዘራ ላይታጨድ።

ምርጫውን በግልጽ እንካፈላለን ብሎ በሁሉም ያገሪቷ ክፍል የምርጫ እንቅስቃሴ አጧጥፎ ለማድረግ። በሰላም እንታገላለን ላሉት ከዚህ የተሻለ አጋጣሚ የለም። ከፈለገ ይሰር፣ ይግደል አሁን ካለበት የውስጥ ችግር ጋር ተደምሮ ግእባተ መሬቱ ይሆናል፡፣ ከተለያያ አቅጣጫ እንዳንጠምደው ምክንያት ልናደርገ እንችል የነበረው። የትግል የትኩረት አቅጣጫ እንዳይበታተን፣ የሰው ሀይል የገንዘብ ሀይላችን እንዳይከፋፈል.... አይነት ቢሆን አግባብ ያለው ምክንያት ነበር፡፡ ችግራችን እሱ አይመስለንም ወያኔ መከላከል ከሚችለው በተሻለ በተለያየ አቅጣጫ ለማጥቃት አቅሙ አለን።

ከፈለገ ወያኔ ምርጫ የሚባል ነገር የለም ይበል። እያደረገ ያለው ግን በዝህ ውጥረት ውስጥ ሆኖ እንኳ እጁን በሌላ አቅጣጫ ዘርግቶ ምርጫው ውስጥ ገብተው ውጤት ሊያመጡ ይችላሉ ያላቸውን ድርጅቶች እየኮረከመ ነው። ከድሮውም የወያኔ ጥንካሬ ይህ ነው። ሁልንም በእንጭጩ ። እኛ ግን አንድ በአንድ ወይንም አንዱን ትተን በሌላ ነው የምንገጥመው። ከችግሮቹ ከአጋጠሙት ቀውሶች እንዲያገግም እድል እንሰጠዋለን። የትኩረት አቅጣጫን ማሳት፣ ማቀጣጠል፣ መነቃነቅ ሲጀምር መግፋታችንን ማበርታት... የሚባል ነገር እኛ ትግል ውስጥ እስከዚህም ነው።

ለማንኛውም አነሳሳችንም ለዝህ ስላልሆነ አራተኛው አገራቀፋዊ ምርጫ ላይ ለመካፈል ያሉብን ችግሮቹ ላይ መፍትሄ ይሆናል ያልነውን እናቀርባለን። አንድ ብንሳሳትም አንፈራም የኛን አቀረብን እንጂ ይህ ተወስዶ ተግባር ላይ ይዋል ከሚል መንፈስ አይደለም የምንደፈረው። ሁለት የተሳሳተ ቢሆንም ትክክለኛውን መፍትሄ ያጭራል። እኛ ከስማችንም ጀምረን መፍትሄ ላይ ለማሰብ፣ ብዥታ ውስጥ ያለ ግን አጋዥ ሊጠቅም የሚችልን አማራጫ ሀሳብ ሳይታይ እንዳይታለፍ ነው። ፍሬ እያሳየ በአለው በሌላኛው ትግል የወያኔ ጉዳይ ከተጠናቀቀ እሰየው። ስሌታችን አልሰራም በትልቁ ተሳስተናል ማለት ነው ። የወያኔን መሸነፍ በርግጠኝነት እስክናይ ግን አረፋፍደን ደግሞ ይህንንም ሀሳብ ማየት ሊያስፈልግ ይችላልና በአለው ቀዳዳ አገር ቤት እየተፍጨረጨሩ ያሉትም ሙሉ በሙሉ በሰላም መታገሉን አቁመናል አላሉምና እስከመጨረሻው የጀመርነውን እንገፋበታለን። ሁለ ገቡን የትግል መንገድ ምርጫ ላደረጉትም ትግሉን ህዝባዊ እያደርጉት በሂዱ ቁጥር ሊጠቅማቸው የሚችል ሀሳብ ይኖረዋል።

## <u>አራተኛው አገር አቀፋዊ ምርጫ ላይ ለመካፈል ተካፍሎም ውጤት ለማምጣት፣ ውጤቱን ለመጠበቅ ያለብን ትልቁ ችግር ግድያ እስር ማስፈራራት ነው።</u>

እነመለስ ግጥም አድርገው ነው የሚገሉት የሚያስሩት ለዛውም ሰበብ አግኝተው። በይበልጥም በስልጣናቸው ከመጣንባቸው ቁጭ ብለው አስበው ለምን አምስት ሺ ወይ ከዛም በላይ ሊሆን ይችላል አንገልም ብለው ቁጥር ወስነው። አስፈሪ እንዲሆን ለምን የአራት አመት ልጅ፣ የሰባ አመት ሽማግሌ ወይ እርጉዝ ሴት ፈልገን አንገልም። አገዳደሉ ዘግናኝ እንዲሆን ምርጫ አቅርበው አወዳድረው ተማክረው ነው የሚገሉት። ማሰር ሀያ ሺ ሰው አግዘው ተመርጠን ነው እያገዛን ያለነው ብለው ነው ያሉት። አሁንም ከዛም በላይ ይሄዳሉ። ማስፈራራት የተቃወማቸውን ብቻ አይደለም ዘመድ አዝማድም አይቀርም። ህጻናት ማገቻ ይዘው እንገላለን እስከማለት የሚሄዱ አረመኔዎች ናቸው። አቶ ታምራትን ላይኔ የሚፈልጉትን በአይፈጽም ልጁን አያርዱትም ብሎ የሚያስብ ከአለ እነመለስን አላወቃቸውም ማለት ነው።

ግን ነብሰ ገዳይ እስካለ ግድያን ማቆም ይቻላል ወይ ነው ጥያቄው?። አይመስለንም። ምርጫውም ተገባ አልተገባ፣ የተቃውሞ ፖለቲካውም ቢቆም እነመለስ መግደል ያሚያቆሙ አይመስለንም። ህዝብ እነሱ ላይ ትኩረት ያደረገ ከመሰላቸው በቦንብ አስር ሀያ ገለን ለምን ሀሳቡን አናስቀይስውም የሚሉ ናቸው። ሱማሌ ለመውረር ሱማሌውች አሸባሪዎች ናቸው ስላሉ አሸባሪ ምን እነደሚመስል ለኛ ለማሳየት አሮጊቶችን አንገት ሰይፈው ሰውን እስከሂወቱ ቤተክርስትያን ውስጥ አቃጥለው ድርጊታቸውን በካሜራ ቀድተው አሳይተውን ነው:: አሸባሪዎች ምን እንደሚመስሉ የመስከረም አስረአንዱን አሜሪካ ላይ የተደረገውን ፍጅት ማሳየት እንደሚቻል እንኳ አይዞርላቸውም ። ፖለቲካ የሚሰሩት ሰው እየገደሉ ነው፣ ቅስቀሳ የሚያደርጉት ሰው እየገደሉ ነው፣አባላት የሚመለምሉት ሰው እየገደሉ እያሰሩ እያስፈራሩ ነው። አነጻጽረን ይሻላሉ እንድንል በገፍ ገድለው ይህን ያደረጉት እነንትና ናቸው ብለውን ነው። መለስና በረከት መግደል በሚችሉበት ሁኔታ እስካሉ ምንም በአናደርግ አይር አብዝታችሁ ተነፈሳችሁ ብለው መግደላቸውን አያቆሙም።

በንጹህ አስተሳሰብ ተቃዋሚዎች እንደገና ምርጫ ላይ ገብተው ሊፈጠር በሚችል የህዝብ መነሳሳት ሊገደሉ የሚችሉ ንጽህንን ሂወት ምርጫው ላይ በአለመሳተፍ ማትረፍ ይቻላል ብለን የምናስብ ክቡር ለሆነው የሰው ልጅ ሂወት ከአለን መቆርቆር ይመስለናል። አብረን ግን እነዚህን ጉዳዮች እንይ። እነመለስ መግደል በሚችሉበት የተመቻቸ ሁኔታ ስላሉ። በአለፉት አራት አመታት በተለያየ ጊዜ ደሀው ኢትዮጵያዊ በሚያዘወትርበት ቦታ በአፈነዷቸው ቦንቦች የሞቱት ንጹሀን ቁጥር ምርጫው ላይ ተገደሉ ከተባሉት ግማሽ ደርሷል። ከባለፈው ምርጫ በኋላ ኢሰመጉ ያወጣቸው ዘገባዎች፣ የአሜሪካን እስቴት ዲፓርትመንት ያወጣቸውን የንጽሀን ፍጅት ብንደምር ቁጥሩ በጣም የበዛል። እራሱን ችለን በነመለስ ህዝብን ከህዝብ ማገዳደል ፖሊሲ በቦረና ዞን የሞቱት ንጹሀን ሀምሳ እጥፍ ያጥፈዋል። ወጣቶች የመጨረሻው ተስፋ መቁረጥ ላይ ደርሰው ለመትረፍ ያላቸው እድል ከሀምሳ በታች መሆኑን እያወቁ ወደየመን በባህር ለመቋረጥ ሲሞክሩ ሰምጠው የሞቱት ስድስት እጥፍ አጥፎታል። በወለጋ እኩል ቁጥር ያለው ንጹሀን ተፈጅተዋል። በጎንደር መሬታችን ለምን ለሱዳን ተሰጠ ስላሉ ቀላል ቁጥር የሌው ህዝብ ተገሏል ተግዟል ተፈነቅሏል። ከዚህ በፊት በጋንቤላ በጎንደር በአርሲ

በአዲስአበባ በሀረር በሌሎችም ክፍለሀገራት ምንም ከምርጫ ጋር ወይ በቀጥታ ስልጣናቸው ለይ ያላነጣጠር ይህዝብ ጥያቄን ላለመመለስ ወይም ለፖለቲካ ፍጆታ ሲባል የፈጁቸውን እንዴት እናየዋለን።

ከንደዚህ አይነፍ ፍጥረቶች ጋር ምርጫ ውስጥ መግባትና ስልጣናቸው ላይ መወዳደር አደጋ እንዳለው የማያውቅ የለም። ምርጫ ላይ ገብተን አሸነፋን ከዛ በኋላ ስለሚሆነው ነገር አይደለም ገና ለገና ምርጫው ላይ መግባታቸው አይቀርም ብለው ከአሁን ጀምረው መግደል ማሰር ማስፈራራት ጀምረዋል። አራተኛው አገራቀፋዊ ምርጫ ላይ መካፈል አለብን ስንል አሁን አይገሉም አያስሩም ብለን ምክነያት መከራከሪያ ማቅረብ እንደማንችል እናውቀዋለን። በአለም ላይ የተበደሉ የተገፉ አርገውት በአያውቁም እኛ የመጀመርያ እንሁንና በተጻራሪው መርጫ በአለመግባት ስልጣናቸው ላይ በአለመወዳደር የነመለስን የመግደል ጸባይ ማስቆም የቻላል ሳይገሉ እንዲገዙ ማድረግ ይቻላል የሚል አሳማኝ መከራከርያ ማቅረብ የሚችል ካለ እንውሰድለታለን። እዚህ ጉዳይ ላይ እንኳን ሌላ ሰው መለስ እራሱ ማረጋገጫ መስጠት አይችልም፡፡ ይህ በንጽህና ምርጫውን ከነመለስ መግደል ጋር ለምናገናኘው ነው። ህዝባችን የሚገሉት ከሆነ እራሱን እየተከላከለ ይሙት የሚለው ሀሳብ አግባብ ነው። አሁን ምርጫ ይገባ ስንል በኋላ እራሱን ችለን የምንመጣበት ቢሆንም ህዝብ ማንም ሊገለኝ መብት የለውም ብሎ መሆን አለበት። ላለመገደል ያለፍርድ ቤት ትእዛዝ ላለመታሰር ምንም ነገር ማድረግ እንደሚችል አውቆ ነው መሆን ያለበት።

እኛ የምንለው ገዳይ እስካለ ግድያ ይኖራል። ግድያን ማስቆም የሚቻለው ገዳዮችን መግደል በማይችሉበት ሁኔታ ሲሆኑ ብቻ ነው። በኢትዮጵያችን አሁን በአለችበት ሁኔታ ምርጫ መፎካከርያ ሳይሆን አንዱ አይነት ትግል ነው። ትግልን ደግሞ ይገላሉ እያልን ማድረግ አንችልም። እንደውም ነብሰ ገዳዮች ስልጣን ላይ ስላሉ ነው እየታገልን ያለነው። እንደሚገሉ እንደሚያስሩ እያወቅንም ነው ምርጫ ውስጥ ገብተን መታገል አለብን የምንለው። የማሸነፍ ሚስጥሩም ያለው እዚህ ላይ ነው። ከሰማንያ ሚሊየን ህዝብ መታገል የደረሰው አርባ ሚሊየን ነው ብንል እንኳ ሁሉም ነፍጥ መያዝ የለበትም። አርባ ሚሊዮኑም ግን መታገል አለበት ብዙ ህዝብ ለማታገል ደግሞ ምርጫ አንዱ መንገድ ነው። የኛ ሀይል ህዝብ ነው። የብዙዎችን ተሳትፎ የሚፈልግ ትግል ወደኋላ ብሎ በቀላሉ ትግሉ ላይ ውጤታማ መሆን አስቸጋሪ ነው። ከተለያየ አቅጣጫ እንዳይወጠር መፍራት ያለበት ወያኔ እንጂ እኛ አይደለንም። እኛ ሶስተኛና አራተኛ የትግል አውድማ ለምክፈትም የሚያስችል በቂ ምክንያትም ፍላጎት ያለው ህዝብም አለን።

ምርጫ የመግባትና ያለመግባትን ውሳኔ አይደለም ትግልን በሚመለከት ማንኛውም ጉዳይ ላይ ይገላሉ ከሚል መሰረት ተነስቶ ብቻ ውሳኔ ማድረግ አይቻልም። ትግል ላይ መሆናችንን ገዳዮች ነግሰውብን እንዳሉ ታሳቢ አድርገን ከብር ከሆነው የሰው ልጅ ሂወት ጋር የሚገናኝ ጉዳይ ስለሆነ ከኛ በኩል ማድረግ የለብን። እንዳይገሉ ማድረግ የምንችለው እንዴት ነው፤ ለገዳዮች ሳንመቻች መታገል የምንችልበት ብለሀት አለ ወይ። ጉዳቱን መቀነስ የምንችልበት መንገድ አለ ወይ የሚል ነው መሆን ያለበት። እኛም በነመለስ መግደል ማሰር ማስፈራራት ላይ ልንል የምንችለው በዚሁ ጉዳላይ ብቻ ነው።

**_በፊት የፈጸሟቸውን ግድያዎች ትናንት እንደፈጸሟቸው እንደሰማቸው እንደሚሰማን ምርጫው እየተቃረበ በሄደ ቁጥር አጠንክረን የምንጠይቅበት የምንቃወምበት ...ማድረግ_**

_የፈለገ ዘግናኝ አገዳደል ቢሆንም ገዳዩም ላይ ድርጊቱም ላይ ጊዜ በጨመረ ቁጥር ስሜቱ እየደበዘዘ ይሄዳል። እንደገና እንዲታወስ የሚያደርገው ነገር ከአልተደረገ። እነመለስ ይህቺን ያውቋታል በደንብም ተጠቅመውበታል። እኛ እንረሳለን እንጂ ገዳዮች አይረሱም ለዚህ ነው እያዘናጉን ደግመው ደግመው የሚገሉት። አሁን አሁን እየተሻለው ሄደ እንጂ እኛም ስንረሳው ፈጣኖች ነን። አሁን በአንጻራዊ ጥሩ ነው ያለው። ጅምሩን አጠንክረን ማሳደግ አለብን። መሆንም የሌለበት ስለሆነ መርሳት የለብንም ሁሌ ጊዜ ወገኖቻችንን ዛሬ እንደፈጁቸው ተሰምቶን እንዲሰማቸው ማድረግ አለብን። ማዘናጋታቸውን መፍቀድ የለብንም። ለምርጫ ቅስቀሳ ሊያደርጉ በሞከሩ ቁጥር ስለግንባታ፤ ስለእድገት፤ ተሳስተን ነበር ሌላ ጉዳይ ላይ እንዲያወሩ በፍጹም መፍቀድ የለብንም። ሁሌ ጊዜ ስለፈጁቸው ወገኖቻችን እንዲያስቡ ማድረገ አለብን። ጽሁፎቻችን፤ ሚዲያዎቻችን፤ ወሬያችን፤ ፖስተሮች፤ የተቃውሞ፤ ሰልፋችን ሁሉ ነገር እንዲያስታውሱ የሚያደርጋቸው መሆን አለበት። የፈጁቸው ንጹህን ፎቶ የቪዲዮ ቅጂ፤ ስምዝርዝራቸው ሁሉም ከተደበቀበት መውጣት አለበት። አገርቤት ሊያየው እድሉን ላላገኘው ሁሉ እንዲያየው መላ መፍጠር አለብን ይህን ብቻ ለመስራት እየተሰባሰቡ ያሉ የስቪክ መሀበራት ሀላፊነቱን መውሰድ አለባቸው፡፡ እስከምርጫው ጊዜ ድረስ ሙቀቱ እየጨመረ በሚሄድ መንገድ ስናደርገው ነው። ገዳዮች ነገ የሚገሏቸው የሚያስሯቸው ላይ አሰብ እንዲያደርጉ የምናደርጋቸው።_

**_ሀ.በተቻለ መጠን የበዛው ኢትዮጵያዊ የመግደል ባህሪያቸውን ትክክል በሆነው ሁኔታ እንዲረዳ ከአሁን ጀምረን እስከምርጫው ጊዜ ድረስ ጠንክረን መስራት።_**

_ይህ ሀሳብ እየታገለ ላለው የነመለስን ሁኔታ በቅርበት ለሚከታተለው ፖለቲካ ውስጥ ላለው ከራሱ እውቀት አኳያ ስለሚያየው መዘባረቅ ይመስላል። እስቲ ስለነመለስ የመግደል ባህሪ፤ ለምን እንደሚገሉ፤ ለምሳሌነት ከላይ ያስቀመጥናቸውን ወይም ሌሎች የፈጸሟቸው ግድያዎችን በዝርዝር ጽፋችሁ ኢትዮጵያዊያን የሚሰባሰቡበት ቦታ ቤተክርስትያንም፤ ቡና መጠጫም ይዛችሁ ጎራ በሉና በጉዳዩ ላይ ያላቸውን አስተያየት ጠይቋቸው። ከስፈለገም ምርጫ አስቀምጡ።_

_ሀ. እነመለስ የፈጸሙት ነው ትክክል ነው። (ግሽግሽ የሚልበት)_
_ለ. ተጋኗል ወይ ፖለቲካ ነው። (አፍሪካ ውስጥ ምኑ ነው እንግዳነቱ)_
_ሐ. አያደርጉም በታሪካችን ከመቼውም ጊዜ በላይ አሁን ሰው ያለህግ የማይገደልበት ነው።( ደግ አደረጉ)_

_እኛ ሀያ ሰዎች ላይ ሞክረነው። ዘጠኙ ትክክል ነው ሲሉ፤ ስምንቱ ተጋኗል፤ ሶስት አያደርጉም የሚል ምላሽ ነው የሰጡት። አስደንጋጭ ነው ግን እውነት ነው። ቀላል ነው ሞክሩት። ተጋኗል ከአሉት ሁለቱ ተቃዋሚ ፖለቲካ ውስጥ ያሉ ናቸው። ጥሩ_

መንግስት አይደለም ያለን የሚለው ሁሉ ጥሩ ያለመሆኑን ደረጃ በትክክሉ የተረዳ አይደለም። አለመረዳት ብቻ ላይሆን ይችላል። ሌሎች ምክንያቶች ሊኖሩ ይችላሉ ግን በየጊዜው የመጥፎነቱን ደረጃ በጥሬው እንዳለ የሚነግረው የሚያስታውሰው የሚያሳየው ቢኖር ኖሮ ቁጥሩ ይህን ያህል በአልበዛ ነበር። ይህን ሲያደርጉ የምናየው የተወሰኑ ግለሰቦችና ቡድኖች ናቸው። ከግለሰቡ የራስ ምክንያት በተጨማሪ ሚዲያዎቻችን የመድረስ አቅማቸው፣ ጉዳዩን የሚያቀርቡበት ቃላት፣ አንድ ድምጽ አለመኖር፣ በፖለቲካው ቅድሚያ የሠጠንባቸው ጉዳዮች የኋላ ታሪካችን፣ በጭንቅላት ሳይሆን በዘሩ የሚያስብ መኖሩ...የብዙ ምክንይች ድምርምር ነው።

የተነሳንበት አላማ የነመለስን የመግደል ባህሪ የበዛው ህዝብ እውነት በሆነው ማወቅ በሚገባው ደረጃ ማወቁ እንዴት የጠቅማል የሚለውን ለማሳየት ስለሆነ ወደዛ እንመለሳለን።

የነመለስ የመግደል ጉዳይ በህሪያዊ ነው። ከአምላክ የተፈቀደውን ለመኖር ግድ የሚለውን ለምግብ የሚሆኑ እንሰሳትን አርደን ስንበላ የሚሰማንን አይነት መጥፎ ስሜት እንኳ ሳይሰማቸው ነው የሚያደርጉት። ከጤና ችግር ጋር ያለ ነው የሚለው ሀሳብ ተአማኒነት እያገኘ የሄደው ለዚህ ነው። የበዛው ኢትዮጵያዊ የመግደል በህሪያቸውን በአግባቡ ከአወቀው እነሱ እስካሉ ግድያው እንደሚኖር ይረዳል፣ ማስወገድ የሚለውን ምርጫው ያደርጋል። ቁርጠኛውን ያበዛል። ትግሉ ላይ ለራሱም ለሌላው ወገኑም ደህንነት ሲል በሀላፊነት እንዲንቀሳቀስ ያደርገዋል። የሚኖሩ የትግል ጥሪዎችን በሀላፊነት በጥንቃቄ እንዲከውን ያደርጋል። ግድያውን ከሚፈጽሙላቸው እንቢተኛው ይበዛል፣ በትክክለኛ መንገድ የሚረዳቸው እየበዛ በሄደ ቁጥር እያገለልናቸው ተነጥለው እንዲወጡ እናደርጋለን። በይበልጥም በጭንቅላታቸው ሳይሆን በዘር ብቻ አስበው ድጋፍ የሚሰጡትን ያሳንሳል። ግንቦት ሰባቶች እዚህ ጉዳይ ላይ በሰሩት ድንቅ ስራ ውጤቱን እያየነው ነው።

ማለት የፈለግነው አንድን ሰው ሌላኛው በጥይት ገደለው ሲባልና አንገቱን አረዱ ነው የገደለው ሲባል ስለገዳዩ የሚኖረን ስሜት አንድ አይደለም። በተመሳሳይ ተጣልተው ገደለው ሲባልና ሰው ሲሞት የሚያሳየውን ሁኔታ ለማየት ፈልጎ አረደው ቢባልም እንደዛው።

## እነመለስ ግድያ ማሰርን ማስፈራራትን ለምን እንደሚጠቀሙበት ማዋቅና መፍትሄ መስራት

መግደል የባህሪያቸው ቢሆንም። ሁሉንም ጊዜ የሚጠቀሙበት ለማስፈራራት ነው። ጉዳዩ የጭንቅላት ጨዋታ ነው። መግደላቸው ማሰራቸው አስፈርቶን የምንፈልገውን ከማድረግ ይገታናል ብለው ስለሚያምኑ ነው እየፈጸሙት ያሉት። አጢነን ከአየነው እንዳሰቡት ፍራቻ ነበር ወይ ትግል ተጀምሮ እንዳይቀጥል የሚያደርገው?። ግድያና እስር ህዝብን ከመታገል የሚያቆም ቢሆን ኖሮ እነመለስ ስልጣን ከያዙ ጊዜ ጀምሮ ከጭፍጨፋ ላይ ጭፈጨፋ እያካሄዱ የሚታገላቸው በአልኖረ ነበር። ትናንት በገፍ

ገለው በሚቀጥለው ቀን ሊቃወማቸው ህዝባችን ወጥቷል። ታስረው የተፈቱት ዛሬም ግንባር ታጋዮች ናቸው። ታስረው የተፈቱ ጋዜጠኞቹም ግንባር ጋዜጠኞች ናቸው፤ ህዝባችንን በትንሹ የአንድነት የሜክሲኮ አዳራሽ ስብሰባ ላይ አይተንዋል ወደፊት ደግሞ ይበልጥ ይታያል። ያለመሪ እየገደሉትም ለስድስት ወር የታገለ ህዝብ ነው።

በመግደል በማሰር የህዝብን ትግል ማፈን ይቻላል አይቻልም የሚለው ላይ ቁርጥ ያለ መልስ መስጠት አይቻልም። እንደገዳዮቹና እንዳታጋዮቹ መሪዎች ችሎታና ዝግጅት ነው የሚወሰነው። የህዝብን ትግል አሸናፊም ተሸናፊም ሊያደርግ የሚችለው ይህ ነው እስከዛሬ በአለም ላይ ከትደረጉ ትግሎች የምንማረው፡፡ እነመለስ እንደሚያስቡት ፍራቻ እዚህ ጉዳይ ላይ ትልቅ ቦታ የለውም።

መግደልና ማሳረቻው የምንፈልገውን የጀመርነውን ከግብ ለማድረስ እንደማያቆመን እንዲያውቁ ግልጽ ሆኖ እንዲታያቸው ማድረግ አለብን። ድርጅታዊ ጥንካሬያችን ትግሉን ለማስቀጠል አቅም ያለን መሆኑ፡ ያደረግነው በቂ ቅድመ ዝግጅት፤ ህዝብና ተቃዋሚዎች የሚፈጥሩት መናበብ.... የመሳሰሉት ብዙ ሊሰራባቸው ልንለማመዳቸው የሚገቡ ጉዳዮች አሉ። ይህ ሲሆን ብቻ ነው መግደላቸው ማሰር ማስፈራርታቸው የህዝብ ትግልን ጥያቄ ማፈኛ መፍትሄ ይሆናል ብለው ማሰባቸውን የሚያቆሙት።

## <u>ትግሉን በኛ የጊዜ ቀመር ማካሄድ ያስፈልጋል</u>

ምርጫ 97 ላይ እነመለስ ለመግደል እንዲያመቻቸው የተጠቀሚት አንድ ብለሀት ትግሉን መምራትን ከቅንጅት እጅ መንጠቃቸው ነው። ከመነሻውም በነሱ የጊዜ ቀመር አስጀመሩት በአንዴ በአገሪቷ ውስጥ በሙሉ እንዳይካሄድ ማድረግ ቻሉ። መሪነቷን ስለቀሙ መግደልንም በገፍ ማሰርነም በሚጠቅማቸው በሚመቻቸው መንገድ እንዲፈጸሙ ሆነ። ያን ጊዜ ቅንጅት መፍጠር የቻለውን ተአማኒነት ከህዝብ ጋር መናበብ ስናየው። ማንም ሰው ያለፍርድ ቤት ትእዛዝ የቤተሰባችሁን የሰፈራችሁን ሰው እንዳያስር መከላከል መብታችሁ ነው ተብሎ ትእዛዝ ተላልፎ ቢሆንስ ኖሮ። ሀያ ሺ ሰው አይደለም መቶ ሰው ማሰር የማያችልበት አስገዳጅ ሁኔታ ውስጥ ወያኔን አስቀምጠነው ነበር። ልጄን መውሰድ አትችሉም ለማለት ሁሉም በአይምሮው ሳይዞር ቀርቶ አይደለም። እሱ ብቻ ወይ የተወሰኑ ሲያደርትጉና ሁሉም አንድ ላይ ሲያደርገው ውጤቱ የትለያየ ስለሆነ አላስፈላጊ መሰዋትነት ላለማድረግ ብሎ ነው። ይህ ትግሉን ከመምራት አኳያ ነው።

ገፍተው ሄደው እንዳሸናፊ እንደመንግስት መናገር ችለው ቢሆንስ ኖሮ። መለስ ቀድሞ እንዳወጀው ለህዝቡም ለጦሩም መመሪያ አስተላልፈው ቢሆንስ ኖሮ። ዛሬ ላይ ሆኖ እርግጠኛ መሆን በአይቻልም በተለየ ሁኔታ እኝን በሚጠቅመን መንገድ ይከናወን ዘንድ ሌላ ምርጫ ነበር ማለት ነው። ሊሰራም ላይሰራ ይችላል እኛ ይሰራ ነበር ነው የምንለው። እነመለስ አይነትን ገዳይ የወያኔ አይነት ውህ ላይ የተሰራ ድርጅት ለማስቆም ተወዳደሮ ጥርት አድርጎ እንደባለፈው ማሸነፍ ከዛም ትግልን አይደለም አገርና ህዝብን ነው መምራት መጀመር የሚያስፈልገው። ለዚህ ደግሞ የምንጠቀምበትን ቃላት መምረጥ፤ መቀየር አለበን። ይህ ከአሁኑ ሊታሰብበት ይገባል። የመሪነቱን ቦታ ስንቀማ ትግሉንም እንደሁኔታው አገርና ህዝብን

መምራትና እኛ በፈልግነው ጊዜ ትግሉንም ማስኬድ ስንችል ነው የነመለስን የመግደል አቅም ሀይል ልናሳጣው የምንችለው።

**ምንም አይነት የተቃውሞ እንቅስቃሴ ላይ ስሜታዊነት ለገዳዮች መመቻቸት እንደሆነ ህዝብም መሪዎችም ማወቅ አለባቸው**

ከመሀላችን አንዱ እንደዚህ አይነት የወያኔ ብለሀት ላይ ገጠመኙን እንዲህ ይገልጸዋል። ወያኔ ስልጣን በተቆጣጠረበት አመት አሁን ስሙን የማያስታውሰው ድርጅት መገነጣጠል የግለሰቦች እንጂ የህዝቦች ፍላጎት አይደለም ብሎ ተነስቶ ነበር። እዛ ሰልፍ ላይ ተካፋይ ነበር ። ሰልፉ ከአቢዮት አደባባይ ነበር የሚጀምረው። የድርጅቱ መሪዎች ሰገነቱ ላይ ቆመው በአንዲራችንን ሲያውለበልቧት የነበረው ውበት ከህዝቡ ጩሀት ጋር ተደምሮ የነበረው ሴሜት ከባድ ነበር። በዚህ መሀል በአማረ ፈረስ ላይ ተቀምጠው በኦሮሞ የባህል ልብስ ያሸበረቁ ሀያ አምስት የሚሆኑ ፈረሰኞች ከአስመራ መንገድ አቅጣጫ ወደሰልፈኛው መጡ። ሰልፈኛው ዘፈኑን ቀይሮ "እዩት ተመልከቱት የህዝቡን አንድነት" እያለ ወደፈረሰኞቹ ሲሄድ ዘግተውት አለፉ ይህ ንዴትን አጫረ። ሆን ተብላ የተቀናበረች ተንኮል ነች። ሰልፈኛው በዛ አይነት ሴሜት ውስጥ እያለ። ከሰልፈኛው አንዱ በጆሮዬ ተጠግቶ ሹክ አለኝ ከጦር ሀይሎች በኩል አንድ ብርጌድ የወያኔ ጦር እየመጣ ነው የሚል። ወሬዋ ሆን ተብላ ሰልፈኛው ዘንድ ሁሉ ተዳርሳለች። ከዛ በኋላ ሁሉችንም ስሜታዊ ሆነን ነበር ቤተመንግስት ስንደርስ መሳርያ ይዞ ቤተመንግስት አጥር ላይ ለተደረደሩ ወያኔዎች ማንም ግድ አልነበረውም። ደም የለበሰ አይናቸውን ተጠግቼ መንካት ያህል አይቼዋለው። በዛን ሰአት ምንም ነገር ቢያደርጉ ግድም የሚሰጠው ያለ አይመስለኝም። የዛን ለት ለምን እንደው እንጃ አልገደሉም። ዛሬ ላይ ሆኜ ሳየው ሰልፉን እነሱ በሚፈልጉት መንገድ መምራት ችለው ነበር።

ቅንጅት የጠራውን የመኪና ጥሩንባ መንፋቱን ተቃውሞ ትንኮሳ አካሂደው ህዝብን ስሜት ውስጥ ከተው ወደ አመጽ ቀይረውት ያለሙትን ግድያ ፈጸሙ። ይህ ሁኔታ እንደሚፈጠር ተገምቶ በዚህ አይነት አጋጣሚ ለወሰዱ የሚገባቸውን ህዝብ ማድረግ የነበረበትን ነገር ተጠቁሞ ቢሆን ወያኔ ወደሚፈልገው ለመግደል ወደሚያመቸው ሰላማዊውን ተቃውሞ አይወስደውም ነበር። ዛሬ ተምረናል ከአሁን ጀምሮ ህዝብን እንደዚህ አይነት ጉዳዮች ላይ ማስተማር አለብን።

መሪዎችም ትግሉን መምራት አለባቸው። ህዝብም ከባለፈው ተምሮ ስሜታዊነት ቦታ እንዳይኖረው መጠንቀቅ አለበት። ትምህርት በዚህና በተመሳሳይ ጉዳይ ላይ ሊሰጥበት የገባል። ለምሳሌ ሁሉ በየደጃፉ ሻማ ማብራት አለበት ተብሎ እንደው ጥሪ የተደረገው። ቢተናኮሱም ዝም ሊላቸው ይገባል። መቀጠል የማያስችለው ሁኔታ ከሆነ አጥፍቶ ወደቤቱ መግባት አለበት። በአንዴ በመላው አገሪቷ የሚካሄድ እስከሆነ ሁሉም ጋር መድረስ ስለማይችሉ ሻማ ማብራቱ ይካሄዳል። ወደሚቀጥለው ሰፈር ሲሄዱ ተመልሶ ማብራት መቀጠልም ይቻላል። ትግሉ ሲጠራም ይህ አይነት አጋጣሚ ከገጠመ ይህን አድርጉ፤ ይህን አታድርጉ ተብሎ ሊፈጠሩ የሚችሉ

*ድንገተኛ ነገሮች በሙሉ ላይ መፍትሄ መጠቆም አለበት።*

*የምናደርገውን ማንኛውንም እንቅስቃሴ ሀላፊነት በተሞላበት ከስሜት ጸድተን ስናደርገው ነው። ለገዳዮች የማይመች እንደውም ፍራቻን በግልባጭ ልንፈጥርባቸው የምንችለው። ጥንቃቄው በራሱ ገዳይ ናቸው ማለት ስለሆነ ፖለቲካል ጠቀሜታ አለው፡፡*

*መረጃ የመሰብሰብና የማስተላለፍ አቅማችን ማጠናከር*

*ጠቅለል አድርጎ ሲታይ ትግሉ ጥሩ መረዳት በአለብት ነው እየተካሄደ ያለው። ከላይ ያነሳናቸውም በቀጣይም የምናነሳቸው ነገሮች ጥሩ ግንዛቤ እያገኙ እንደሆን እናውቃለን። መረጃን የመሰብሰቡና የማስተላለፉም ጉዳይ እንደዛው። ከሚያስፈልገን አኳያ ግን ገና ምንም አልተሰራበትም። ከምርጫ 97 በኋላ እነመለስ የፈጸሙትን ጭፍጨፋ ብናይ የተወሰኑ ጀግኖች ጥረት በአይኖርበት የተፈጁትም የተጋዙትም ስም የሌላቸው ቁጥር ያውም እርግጠኛ ያልሆነ ነበር የሚሆኑት። ተሰብስበው የተጋዙት ስም ዝርዝር፤ ትክክለኛው ቁጥር አሁንም የለንም። ግድያውን በአጣሩት ጀግኖች ምክንያት የትወሰኑ የተገደሉትን ሰዎች ስም ዝርዝር ማግኘት ችለናል። የንጹሀን ደም የሚባለው አይነት ነው የሆነው። በግለሰብ ደረጃ ብልህ በሆኑ ጀግኖች አስገራሚ የሆኑ ፎቶዎችና የተወሰኑ ቪዲዮዎች ማግኘት ችለናል። ይህ ግን ስራ ብለን ሰርተነው አይደለም። ያኔ የተገኘውን አጋጣሚ ነገ ላናገኘው እንችላለን። እውነት እንናገር ከተባለ ወያኔ ከፈጸማቸው መጠነ ሰፊ ጭፍጨፋዎች አኳያ ምንም የለንም ማለት ይቻላል።*

*ስለመረጃ ሲነሳ አሁን በመጠኑ እየተሻሻለ ሄደ እንጂ ተቃዋሚዎች የተገደሉባቸውን የታሰሩባቸውን አባላቶቻቸውን እንኳ በስም መቼ እንዴት እንደተፈጸመ ማስቀመጥ ሲሳናቸው ብዙ ጊዜ ታይቷል። ወያኔዎች እራሳቸው በደፈናው ተገደሉብን ታሰሩብን ተስፈራሩብን ይላሉ እንጂ ማቅረብ አልቻሉም ብለው ደጋግመው ሲከስውቸው ይሰማል። እንደዚህ አይነት ሁኔታዎች ናቸው ለገዳዮች አድርገውት ሳይታወቅ ማለፍ እንችላለን ብለው እንዲያስቡ የሚያደርጋቸው።ማድረግ ያለብን*

*-እንደ ኢትዮጵያ ሰባዊ መብት ያሉ ድርጅቶችን በሰው ሀይል በገንዘብም ማጠናከር።*

*-ህዝብ በሙሉ መረጃን እንዲሰበስብ መረጃ እንደሚያስፈልግ ጥሪ ማድረግ መረጃውን ማስተላለፊያ መስመሩን መጠቆም። የሚያስፈልገንን የመረጃ አይነት ግልጽ ማደረግ።*

*- በውጪ በየአገሩ ተበትኖ ያለው ህዝብ ከያንዳንዱ ያገራችን መንደር የወጣ ነው። ሁሉም በየሰፈሩ የሚገደሉትን የሚታሰሩትን መረጃ ማግኘት ይችላል። ይህንን ሀይል ለመጠቀም መሞከር።*

*-ህዝባችን መረጃን ለመያዝ በአብዛኛው እጅ ያለውን የሞባይ ስልክ መጠቀም*

ጀምሮ ያለውን የፎቶ፣ የተንቀሳቃሽ ሰእል መቅረጫውን እንዲያዘጋጅ ጥሪ ማድረግ። ይህን ሁሉ ማድረግ ከአልቻለ ያየውን የሰማውን ሁሉ በተሟላ መንገድ በአግባቡ እንዲመዘግብ ማድረግ።

- እንደኢትዮጵያዊያን መወያያ መድረክ አይነት ብዙ ህዝብ ከተለያየ ያገራችን ክፍል የመጡ የሚካፈሉበት ከታሰበበት የኢትዮጵያን ካርታ አስቀምጠው፣ ከዚህ ቀበሌ ከዚህ አውራጃ ማግኘት የሚችል እያሉ እንደቀልድ ሁሉም ቤተሰቡ ጋር እየተገናኘ የየሰፈሩን መረጃ እንዲሰበስብ ማድረግ ይቻላል። ሊሰራ እየፈለገ ምን እነደሚሰራ ግራ ለገባው ትልቅ ስራም ይሆናል።

-አገር ቤት ያሉ ተቃዋሚዎችም ይህን የሚሰራ አንድ መአከል ማቋቋም አለባቸው። በውጪም ከተቻለ ድርጅቶች ያለበለዚያ የስቪክ መህበራት በተገኘው ላይ መስራት ላይ ብቻ ከሚያተኩሩ እጃቸውን ወደ ኢትዮጵያ ዘርግተው መረጃ መሰብሰብ መጀመር አለባቸው።

-ሁለት አይነት የመረጃ ማስተላለፊያ መንገድ መፈጠር አለበት። ከያንዳንዱ መንደር-- ወደ አገርቤት ያሉ ተቃዋሚዎች ወደ ሚፈጥሩት ማእከል-- ከዛ ወደወጪ ወደሚቋቋመው መአከል። ከእያንዳንዱ መንደር-- ወደ ውጪ-- ከዛም መልሶ ወዳገር ቤት።

ለምንጽፍበት ጉዳይ በአይጠቅምም ዛሬ አገር ቤት የደወለ ሰው እናዳገኘው መረጃ። አንድ ሰው ከውንጀል ነጻ መሆኑን ማረጋገጫ ወረቀት ለማግኘት ለሊቱን ተሰልፎ ማደር አለበት። የተደወለለት ሰው ሰልፉ ላይ ያደረ ነበር። የሰልፉን እርቀት ሁለት ማይል አካባቢ ይደርሳል ብሏል። ይህ መረጃ ለሌላ በአይሆን ለፕሮፓጋንዳ ፍጆታ ይሆናል።

ሁሉም የአገሪቷ ቀበሌ የሚደርስ፣ ፈጣን ፍሰት ያለው የመረጃ ዝውውር ገዳዮችን ቆጠብ እንዲሉ ያድርጋል። የገዳዮች ሁሉ ባህሪ ገድለን አስረን ሳይታወቅብን እናልፋለን ነው።

<u>ጥንቃቄ</u>

ህዝብ ቀድሞ ማድረግ የሚገባውን ጠቅላላ ጥንቃቄዎችን ማወቅ አለበት። ስከስሜታዊ ድርጊቶች ስለመቆጠብ። የሚሰጥ የትግል መመርያን በተሰጠው መመርያ መሰረት ስለመፈጸም። ድርጊታችን ለኛም ለሌላውም ወገናችን ለገዳዮች የሚመች ስለማይሆንበት ሁኔታ፣... የመሳሰለ።

መሪዎች የሚያወጧቸው የትግል ጥሪዎች ላይ ሁሉ መወሰድ ስለሚገባቸው ጥንቃቄዎች ሊፈጠር የሚችል አጋጣሚ ሁሉ ታስቦበት ህዝብ መውሰድ የሚገባው ጥንቃቄ መገለጽ አለበት። የቅንጅት መሪዎች ወያኔዎችን ከመህበራዊ ተሳትፎ ማግለል ላይ እንዳስቀመጡት ጥንቃቄ። የመኪና ጥሩንባ መንፋቱም ላይ ማስቀመጥ ይቻል ነበር።

## ምክንያት ስተሰጠበት ብቻ አንድን ነገር ትክክል ነው ብሎ መቀበል መተው።

በአንጻራዊ አሁን እየተሻለው መጣ እንጂ ለወያኔ ቁርጥ አድርገን ያልከለከልነው ወይ ልናደርገው ያልቻለነው ነገር ለሚያድርጉት ጸያፍ ስራ ምክንያታቸውን አለመቀበልን ነው። በዚህ ችግር አይደለም ህዝቡ ተቃዋሚዎች ሲሸወድ ብዙ ጊዜ ታይቷል። ለምሳሌ- ወያኔ ሱማሌ ሲዘምት እስላም አክራሪዎች አገራችን ላይ ጅሀድ ስላወጁ ላጠፋ ነው ያለውን ምክንያት የገዙለት ነበሩ የመጨረሻ ውጤቱ ወንድሞቻችን እሬሳ በሰው አገር አስጎትተን እሱ ግን ለስልጣኑ ዋስትና ሆኖት ነው የወጣው፤ የኤርትራው ጦርነት ጥሩ ምሳሌ ነው። የዘጠና ሰባቱን ጭፍጨፋም ድርጅትን ወክለው ትክክል ነው ያሉ ነበሩ። በየግዜው ቦንብ አያፈነዳ የጨረሳቸው ንጹሀን ላይ የተሰጠውን ምክንያት አንዳንዶች ሲገዛለት ታይቷል።

ወደ ህዝብ ስንመጣ ደግሞ ችግሩ ጎልቶ የታያል። አንዳንዴ እነመለስ ሳይጨነቁ የሚሰጡትን ፍጹም የውሸት ምክንያት አይተን ግርም የሚለን ሰዎች ከአለን ምክንያታቸውን ሙሉ በሙሉ በአይቀበለውም በከፊል የሚወስድ ህዝብ እንዳለ ስለሚያውቁ ነው። በቅርብ እንኳ ወ/ሪ ብርቱካን በግፍ መታሰሯ ላይ የሚሰጥ ሀሳብ ጥሩ ምሳሌ ነው። ይህም ብቻ አይደለም መለስ ያላትን ማድረግ ነበረባት አልነበረበትም የሚለው ላይ መነጋገር በራሱ በተወሰነ ደረጃ አጸያፊ ተግባራቸውን ትክክል ያደርገዋል። በድርጅትም በግልም ስንወስንም ስንጽፈም ስናወራም የምንጠቀምባቸው ቃላት ላይ ጥናቃቄ ከአላደረግን የነመለስን መግደል ማሰር የሰውን ልጅ ማንገላታት እየደገፍን እያበረታታናቸው መሆኑን ማጤን አለብን።

ምንም ነገር ላይ ምክንያት መስጠት በራሱ ጉዳዩን ትክክል አያደርገውም። ምክንያቱ ትክክልና ህጋዊ እስካልሆነ። በዚህ አለም ላይ ምንም ነገር ምክንያት የማይሰጥበት ነገር የለም ደርግም ያን ሁሉ ወጣት ሲጨፍጨፉ ምክንያት እየሰጠበት ነበር። አንድ ሰው ተነስቶ እየተጫወቱ ያሉ አስር ህጻናትን እያባረረ በገጀራ ጨፍጭፎ ገደላቸው እንበል ምነው ሲባል ተኝቼ ጩሀታቸው ረበሸኝ። ብዙ ጊዜ እዝህ አትጫወቱ ብያቸው ነበር ብሎ ምክንያት ቢያደርግ ይህን ምክንያት ምክንያት ነው ብለን የምንቀበል አለን?። እውነቱ ወያኔ ስልጣን ከያዘ ጀምሮ ላደረጋቸው ግድያዎች እስሮች ማንገላታቶች የሚሰጠው ምክንያት የሰውዬውን አይነት ነው። ግማሹ በጭንቅላቱ ሳይሆን በዘሩ እያሰበ፤ ሌላው ለሆዱ፡ አንዳንዴ ለግዚያዊ ፖለቲካ ጥቅም፤ የበዛው የዋሁ ደግሞ መንግስት ስላለው በከፊልም ቢሆን ትክክል ሊያደርገው ስለሚሞክር ብቻ ነው። እንደነዚህ አይነት ፍጡሮች ከጠቅላላው ማህበረሰብ እያነሱ ከአልሄዱ አገራችን የነመለስ አይነት ገዳዮችን መሸከም የምትችል ሆና ነው የምትቀጥለው። ሌሎቹን ትተን መንግስት ስላለው በከፊልም የነመለስን አይነት ምክንያት የሚገዙት ላይ መስራት አለበት። ያኔ ነው የነመለስ ንጹሀንን የመግደል የማሰር የማንገላታት ባህሪ ላይ ተጽኖ ማድረግ የምንችለው፡፤

## ብርቱካናዊ ቀለም ያላት መጸሀፍ ታስፈልገናለች

ተቃዋሚዎች ማድረግ የሚገባቸውን ቡዙውን በድርጅታዊው መንገድ መጠቆም ይቻላል። እነሱም ብቃቱ ተሚክሮውም አላቸው ያስቡበታል። ለህዝብ ግን በኋላ

ሁኔታውም ላይመች መንገዱም ላይኖር ይችላል። ስለብርቱካናማዋ መጸሀፍ እራሱን ችለን የምንልበት ቢሆንም። ስሟም፤ ቀለሟ ብርቱካናማ ቢሆን እንመርጣለን። ብዙ ገጽ የሌላት ሌላው መንገድ ቢጠፋ በጅ ጽሁፍ እየተገለበጠች መዳረስ የምትችል። ዝባዝንኬ ያልበዛባት ሁሉም ኢትዮጵያዊ ሊያገኛት የሚገባ ሸምድዶ ሊይዛት የሚችል፤ ስርቻ ውስጥ ሊወሸቃት የሚችል። ህዝብ ደረጃ በደረጃ ምን ማድረግ እንዳለበት። መውሰድ የሚገባውን ጥንቃቄ ፤ መርጃ የሚያቀብልበትን አድራሻ የያዘች የትግል መጸሀፍ ታስፈልገናለች። ይህን አገር ቤት ያሉ ተቃዋሚዎች ላያደርጉ ይችላሉ መለስ በፈቀደልን መንገድ አንታገልም ብለው አማራጭ የትግል መስመር የተከተሉት ሊያደርጉት ግን ይችላሉ ማንም ስለ ትግል እውቀት ያለው ሰው ሰርቶ ሊያቀርበው ይችላል።

መለስ በአንድ ዙር የገደለውን ያህል ላልገደለ ጉንፋን ለመከላከል እጃችሁን ታጠቡ ስታስሉ አፋችሁን ሸፍኑ… ተብሎ ትምህርት የሚሰጥበት አለም ላይ እየኖርን ያለነው። በየቤታችን በሽታው ምን እንደሆነ እንዴት እነደሚተላለፍ፤ ምን አይነት ጥንቃቄ ማድረግ እንዳለብን በጽሁፍ እየደረሰን ነው። ሌላው ቢቀር እነመለስን እናውቃቸዋለን፤ ህዝብን ከህዝብ ለማናከስ እየሰሩ እንደሆነ እናውቃለን ። ሁላችንንም ያሰጋናል። ይህቺ መጸሀፍ በተወሰነ ደረጃ የዚህ አይነት አደጋን ለመከላከል ትረዳለች። እኛ ግን ህዝብ ቀድሞ የሚያደርገውን የሚደረግበትንም ከአወቀ በመግደል በማሰር አሰፈራርቼ መንግስት ሆኜ ለመቀጠል እንደባለፈው እንችላለን ብለው ገዳዮች እንዳያስቡ ታደርጋለች ብለን ለሁኑ ለመፍትሂነት ያመጣናት።

<u>ግድያውን ይፍጽምልናል ብለው የሚተማመኑበትን አካል ማናገር መድረስ መቻል</u>

የስከዛሬ ትግልችን ላይ መለዮ የለበሰውን በኛ ግምጋሜ እስካሁንም ልንደርሰውና ከኛ ወገን ልናደርገው አይደለም እስከጭራሹ አናግረነውም አናውቅም። ለኢትዮጲያ ሰራዊት ተብሎ አልፎ አልፎ የሚተላለፈው መለክት ማናገር ነው ሊባል አይቻልም። የመስማቱም ጉዳይ እንዳለ ሆኖ ቢሰማስ በዛ አይነት መልክት ምንድን ነው የሚያደርጉት። እኛ የምናየው ለህዝብ በደሉ ይብቃህ መታገል መነሳት አለብህ ብለን ስንነግረው እንደነበረው ነው። ማናገር በሚገባን መንገድ ህዝብን ያናገርነው ምርጫ 97ላይ ነው ውጤቱን ደግሞ ያኔ አይተንዋል። እኛ ማናገር የምንለው ሊያደርግ የሚችለውን አማራጮችን፤ እንዴት መቼ እንደሚያደርጋቸው፤ መብቱን ግዴታውን ተአማኒ በሆነ ድምጽ መናገር ሲቻል ነው። ውጪ ያሉትም በሰላም እንታገላለን ብለው እየተፍጨረጨሩ ያሉትም የተባበረ ተአማኒ ሀይል ያለው ድምጽ መፍጠር ከቻሉ ማለት ነው። ቅንጅት በደንብ ፈጥሮት ነበር። አሁን ደግሞ ግንቦት ሰባት ጥሩ እድገት እያሳየ ነው።

ምርጫ 97 ላይ ህዝብን ለመድረስ ከተደረገው ጥረት አኳያ ጦሩን ለመድረስ ምንም ሙከራ አልተደረገም። ጦሩ የአገር መከላከያ ሰራዊት ሆኖ እንደሚቀጥል ፕሮግራማቸው ላይ ከተቀመጠው ውጪ። ይህንንም እንኳ በተገኘው የመደመጥ እድል ለጦሩ አልተነገረውም። ለምሳሌ በተገኘው የመደመጥ እድል እንዲህ ማናገር በዚህ መንገድ ጦሩ ጋር ለመድረስ ተደጋግሞ ተሞክሮስ ቢሆንስ ኖሮ።

ቅንጅት የኢሀዲግ መንግስት ከአስራስድስት አመት በኋላ ድፍረቱን አግኝቶ እንከን የሌለበት ምርጫ ለማካሄድ ፍቃደኛ መሆኑን ሲገልጽ። የኢሀዲግን ይህን ውሳኔ እናደንቃለን ደስተኞችም ነን። በዚህ ድፍረትን የሚጠይቅ ትክክለኛ የኢሀዲግ ውሳኔ ደስተኛ መሆን ያለብን እኛ ብቻ ግን አይደለንም መላው የኢትዮጵያ ህዝብ በይበልጥም ህግ አስከባሪው አካል ነው። የኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት ፤የፖሊስ ሰራዊት በፍርድ ሂደት ውስጥ ያላችሁ በሙሉ። እንኳን ደስ ያላችሁ።

ደስታችን አገርና ህዝብን ለማገልገል ከህዝቡ ወታችሁ። ከናንተ በፊት እንደነበሩት ሁሉ ቃለ መሀላ ገብታችሁ በንጽህና ትክክል በሆነው መንገድ ለማገልገል የጦሩም የፖሊስ ሰራዊቱም የፍትህ አካሉም አባል እንደሆናችሁ ስለምናውቅ ነው። ይህን ለማድረግ ግን እስከዛሬ አልቻላችሁም ችግሮች ነበሩባችሁ። በአገራችን መንግስትና ህግ አስከባሪው ሊለይ አልቻለም ነበር። ለመንግስት ተጽኖ ውጪ ሆኖ አያውቅም። ዛሬ ኢህአዲግም እኛም እንከን የሌለው ምርጫ ለማድረግ ስንስማማ ፖለቲካውን ለሚወዳደሩ ፓርቲዎች ትታችሁ ገለልተኛ ሆናችሁ እንድታገለግሉ ሙሉ ነጻነቱን ሰጠናችሁ ማለት ነው። ለምርጫው ብቻ አይደለም ከዚህ በኋላ ከፖለቲካው ነጻ ናችሁ ማለታችን ነው። ዛሬ የደረስንበት ደረጃ ለመድረስ እናንተም ከናንተም በፊት የነበሩ የጦሩ ሰራዊት አባላት፤ የፖሊስ ሰራዊት አባላት የፍትህ አካል ውስጥ ያሉ ስልጣን ላይ ላሉ አገልጋይ ላለመሆን ብዙ መስዋትነት ከፍለውበታል።

ከዚህ ምርጫ በኋላ እኛም ኢህአዲግም ሌሎቹም ድርጅቶች በምርጫው አብላጫ ድምጽ ማግኘት ማሸነፍ እንደቻልነው እንቀያየራለን። የመከላከያ ሰራዊቱ የኢትዮጵያ ሰራዊት ሆኖ ይቀጥላል ማለት ነው ። የፖሊስ ሰራዊቱም የኢትዮጵያ የፖሊስ ሰራዊት ሆኖ ይቀጥላል ማለት ነው። ፍርድ ቤቶችም በሙሉ ነጻነት መስራት ትችላላችሁ ማለት ነው።

እንከን የሌለበት ምርጫ አደርጋለው ሲል ኢህአአዲግ እዚህ ምርጫ ላይ እንደ አንድ ድርጅት ሆኜ ነው የሚወዳደረው ማለቱ ነው። እኛም ኢህአዲግም ምርጫውን ለማሸነፍ፤ ውጤቱን ማናችንም በሚጠቅም መንገድ ለመቀየር ህግ አስከባሪውን ለመጠቀም ስልጣን የለንም ማለት ነው። ይህንን ማድረግ የሚሞክር አካል ከህገ መንግስቱን ተላልፏል ማለት ነው። ህጉን ለማስከበር የምትወስዱት እርምጃ ቃል የገባችሁለት ግዴታ እየተወጣችሁ ነው ማለት ነው፡፤

ሁላችሁም ተስፋ እንደምታደርጉት ይህ ምርጫ እንከን የሌለበት እንዲሆን ከኛ በኩል ያለውን ድርሻ ለመወጣት ቃል እንገባለን። የተሻለ ፕሮግራም ይዘን ስለቀረብን እናሸንፋለን ነገር ግን ተሸናፊዎች እኛ ከሆን ምንም ችግር የለም። ሽንፈታችን ተቀብለን አሸናፊውን አካል እንኳን ደስ ያለህ ብለን አሸናፎ በሚያዘጋጀው ዝግጅት ላይ ተገናኝተን ተጨባብጠን የሚያልቅ ነው የሚሆነው። ይህ በኝ በኩል ቃል ለናንተም ለኢትዮጵያ ህዝብም ቃል የምንገባው ነው፡፤

ማናችንም ግን ተወዳድረን የህዝብን ምርጫ ላለመቀበል የምናንገራግር ከሆንን ህብረትም፤ ኢህዲግም ሊሆን ይችላል ህግ ተጥሷልና ህግ አስከባሪው ህግን የማስከበር ግዴታ አለበት። ህዝብ ድምጹን ለማስከበር ህገመንግስቱ በሚፈቅድለት

*መንገድ በሚያደርገው ትግል መብቱ መሆኑን አውቃችሁ ገለልተኛ መሆን ያለብን ገለልተኛ፤ አገልግሎታችሁ የሚፈለግባችሁ ግዴታችሁን መወጣት አለባችሁ። እኛ እውነቱን እንነግራችሁኣን በገዢው ፓርቲ በኩል ፍላጎቱ አለ እንጂ በተጨባጭ ነጻ ሆነን ምርጫው ላይ ለመስራት ችግሮች አሉብን። እዚህ ምርጫ ላይ ስንገባ በሁለት ነገር ተማምነን ነው። አንድ ህዝብ ከገዢው ፓርቲ የተሻለ ፕሮግራም የዘን ስለቀረብን ይመርጠናል። ድምጹንም የማስጠበቅ አቅም አለው። ሁለት ህግ አስከባሪው ከህዝብ የወጣ ስለሆነ የህዝብን ድምጽ ያለማክበር ፍላጎት እንኳ ቢኖር ህግ አስከባሪው አካል ለማስገደድ ነጻ ነህ ከተባለ ሀላፊነቱን የወጣል ለዚህም እውቀቱ ዝግጅቱ አለው ብለን ነው። እነዚህን ጉዳዮች ገዢው ፓርቲም የሚስማማበት ነው የሚመስለን። መቼም ተወዳድሮ ከተሸነፈ ያለህዝብ ምርጫ ስልጣን ላይ እንድቀጥል ለኔ ከአልሰራችሁ አይልም።“*

*በተጨማሪ እኛ ብንመረጥ ህግ አስከባሪው ነጻነቱ እንድናከብር፤ በስራው ጣልቃ እንደማንገባ፤ ጥቅማጥቅምች ያሉበት፤ ያሉባቸውን ችግሮች እንዴት እንደምንቀርፍ ፖሊሲ መንደፍ ነበረብን። ብዙ ሙህራኖቻችን ከውጪም ከውስጥም ቢናገሩበት ቢጽፉበት ቢያስተምሩበት ለነመለስ ክፉ አካሄድ ይሆንባቸው ነበር፡፡*

ዛሬም መለዮ የለበሱት የየትሞርቅ ፤ የወሮ መብራት ፤ ያድክሲቱ፤ የከድጃ ልጆች ናቸው። ለመብቱ የሚቆም ህዝብ እንዲኖር እንደሰራነው። ከዚሁ ህዝብ የወጣ ስለሆነ መብቱንና ግዴታውን የሚያውቅ ህግ አስከባሪ እንዲኖር መስራት አለብን። መለስ ዜናዊ ስልጣን ላይ ለመቆየት እሬሳውን በሰው አገር የሚያስነትተው ሰራዊት። የሰባት አመት ህጻን የስልሳ አመት አሮጊት እንዲገድል የሚያደርገው ፖሊስ ለራሱ ያልቆመ ለኛ እንዲቆም መጠበቅ የለብንም። ህግ አስከባሪ መሆን ማለት ምን እንደሆነ ማስተማር አለብን። ልናናግረው ልንረዳው ለንደረሰው መቻል አለብን። ስናናግረው እንደ አንድ ግኡዝ ነገር ሳይሆን ከፍትለፊታችን ወንበር ላይ ተቀምጦ እንደምናወራው ወንድማችን ልናወራው የገባል። እንደዚህ አይነት ነገር ላይ የማውቅ ጉዳይ የለበትም የምንል ተሳስተናል። ስንቶቻችን ነን አገር ቤት ሆነን ፖሊስ ወይ ወታደር ዳኛ መሆን ምን ማለት እንደሆነ የምናውቀው ነበር። የዳኝነቱን ስራ ላይ ያሉትን ሳይጨምር ህግ አስከባሪው ውስጥ ያሉት ዶክተሮች አካውንታንቶች ኢንጅነሮች አይደሉም ብዙዎቹ ይህ ነው የሚባል ትምህርት የሌላቸው ናቸው። በአንድ መንግስት ውስጥ የስራ አስፈጻሚው፤ ህግ አውጪው፤ ህግ አስከባሪው የየራሳቸው ስልጣን ኖሯቸው እንደሚሰሩ። ውጪ ያለነውም አንዳንዶቻችን በያለንበት አገር ዜጋ ለመሆን ስናጠና ነው ያወቅነው።

**ምርጫ ላይ የሚሳተፉ ተቃዋሚዎች ነገሮችን ትክክል እንዲከናወኑ የማስደረግ አቅሙን ለህዝብ መልሰው መስጠት አለባቸው። ሀይሉ ያለው ህዝቡ ላይ ነው።**

ከባለፈው ምርጫ እንደተረዳነው ከቅንጅት ብዙ መጠበቅ ነበር። ይህ አንድም ህዝብ ተቃዋሚ ድርጅት ማለት ላይ ካለው ጠቅላላ እውቀት ሌላው ቅንጅቶችም ሀላፊነትን በትክክል ደጋግመው ሀይሉ ወዳለው ሀላፊነቱን ወደህዝብ መወርወር ማሳወቅ ስላልቻሉ ሊሆን ይችላል ። አሁንም ማድረግ የሚችሉት ተወዳድረው ማሸነፍ ነው። ድምጹ ከተሰረቀ በአግባቡ ከአልተቀጠረ ለመራጩ ማሳወቅ ነው። ድምጹን የማስመለስ የመረጬ ህዝብ ግዴታ ነው። ለማስመለስ በሚያደርገው ትግል

ለመምራት ከባለፈው በተሻለ ሁኔታ መዘጋጀት ነው የነሱ ድርሻ። አቅማቸው ምን ድረስ እንደሆነ ሊያደርጉ የሚችሉት ውስን እንደሆነ። የበዛው ሀላፊነት ሀይሉም መራጩ ላይ እንዳለ ደግመው ደጋግመው ሊነግሩት ይገባል።

በአሁኑ ምርጫ እውነተኛ ተቃዋሚዎች ከገቡ እዚህ ላይ ደጋግመው ህዝብን ለማስተማር ጥሩ አጋጣሚው አለ። በየሄዱበት ከህዝብ በተገናኙ ቁጥር የሚገጥማቸው ጥያቄ ይገላሉ፣ ያስራሉ፣ ድምጻችንን ይሰርቃሉ የሚል እንደሆነ ጥርጥር የለውም። መልሳቸው መሆን ያለበት እና ምን የደረግ ነው ። ይገላሉ፣ ያስራሉ፣ ይሰርቃሉ ብለህ ድምጽህን ስጣቸው ልንልህ አንችለም። ላለመገደል ላለመታሰር ብለህ ያላመንክበትን ነገር አድርግ ወይ ማድረግህ ትክክል ነው ልንልህ አንችልም። ማንም ስለቻለ ብቻ ሂወትህን ሊያጠፋ ወይ ያለፍርድ ሂደት ሊያስርህ መብት አለውም ልንልህም አንችልም። በህጋዊ መንገድ ከአልሆነ ላለመገድል ላለመታሰር እራስህን መከላከልም መብትህ ነው።፡የሚመራህን በድምጽህ መምረጥ መብትህ ነው። ድምጽህ በአግባቡ መቆጠሩን ማስተማመኛ ማግኘት መብትህ ነው። ድምጽህ ከተዘረፈም ለማስመለስ መታገልም መብትህ ነው። አይነት መሆን አለበት፡፡ይህ በሰላም ለሚታገሉት ሲሆኑ በአሁኑ ከዚህም በተሻለ መነገር በሚገባው ለህዝብ ለመንገር፣ ገፍቶም የሚፈለገው ቦታ ሊያደርሰው የሚችል ሀይል ችግር የለብንም።

ህዝብ የመጨረሻውን ቁርጡን አውቆ ምርጫው ላይ እንደተሳተፈ ሲያውቁ ይህን ሁኔታ በአግባቡ የሚጠቀምበት የተዘጋጀ ሀይል እንዳለ ሲያውቁ ነው እንመለስ ቆም ብለው አሰብ ማድረግ የሚጀምሩት። በአለፈው ምርጫ ያደረጉት መስረቅ መግደል ማሰር ዛሬ እንደማይሰራ የሚገባቸው። ለነገሩ እንሱ አደጋውን አውቀውታል። እዛ ደረጃ ከደረስነው አሁን ሊቋቋሙን እንደማይችሉ ገብቶቸዋል። ለዚህ ነው አሁን ጠንክረው እየሰሩ ያሉት። ሳይቃጠል በቅጠል ነው እስትራተጃቸው። ለዚህ ነው እኛም አሁኑኑ ማቀጣጠል የምንለው።

አንባቢዎቻችን በዚህ ጽሁፋችን የምርጫ 97 ደጋግመን የምናነሳውና ቅንጅት እንዲህ ቢያደርግ ኖሮ የምንለው ትናንት የተሰራውን ዛሬ ላይ ሆነን ለመተቸት አይደለም። ምርጫ 97 መነሻ የሚሆን አንድ ድንቅ፣ ስራ ቅንጅትም ሳይጠቀስ የማይታለፍ ትልቅ ታሪክ ያለው ስለሆነ ነው። ያኔ መደረግ የነበረበት ነገር ከአልተደረገ ጥፋተኞቹ እኛም ነን። ትናንት እኛም ነበርን እንዲድረግ ቀድመን ማሳወቅ መስራት ነበረብን። አይደለም ትናንትን ዛሬ ላይ ሆነን ለነገ ይጠቅማል የምንለውን ስናቀርብ። ተቀባይነት በአያገኝና ግን ትክክል ብንሆን። አሁንም ጥፋተኛ እኛ ነን የሰራል ብለን ያመንበትን ተቀባይነት እንዲያገኝ በአግባቡ አላቀረብንም ወይም ተቀባይነት እንዲያገኝ አብሮ መሰራት ያለበትን ስራ አልሰራንም ማለት ነው። ስለዚህ ያለፈ ላይ አናለቅስም። እያደረግን ያለነው ከትናንት አሁን በአለንበት ሁኔታ ውስጥ የሚሰራውን ወስደን ለነገ ይጠቅማል የምንለውን ሀሳብ እንዲገዛ ተቀባይነት እንዲያገኝ መጣር ነው፡፡

አራተኛው አገራቀፋዊ ምርጫ ላይ ለመካፈል ያሉብንን ችግሮች በዚህ በኩል ብንመለከተው፣ እነዚህን ስራዎች ቀድመን ብንሰራ ልናስወግደው ልናቀለው ይችላል ብለን የታሰቡን ጉዳዮች ላይ እያንዳንዳቸውን ችግሮች እያነሳን የኛን የምንልበት

ነው። ለዛሬ የነመለስን የመግደል የማሰር ማስፈራራት ችግር ምርጫው ላይ የምንካፈል ከሆነ ችግሩን በዚህ መንገድ ብንቀርበው ይጠቅማል ያልነውን ሀሳብ አቅርበናል። ከላይ ሰሞኑን የተነሳውን ጉንፋን አስመልክቶ ፕሬዘዳንት ኦባማ የተናገሩትን ያስቀመጥነው ያለነገሩ አይደለም መፍትሄ ብለን ያስቀመጥናቸው ብዙዎቹ ነገሮች ስናስል እፋችንን በመሀረብ መሸፈን እንዳለብን፤ እጃችንን ቶሎ ቶሎ መታጠብ እንዳለብን አይነት መሆናቸውን ስለምናውቅ ነው። ብዙ ጌዜ ለችግሮች መፍትሄ የማናውቀው ውስብስብ ነገሮ ብቻ አይደለም እያወቅነው ልናደረገው እየቻልን ችላ የምንለው ቀላል ነገሮችም ሊሆን ይችላል።

ሚቀጥለውን ምርጫ በሚመለከት መባል ስላለበት የኛን አለን እንጂ። በዚሁ አይነት፤ በዚሁ ስሜት ነው ሌላውም አይነት ትግሉ ውጤታማ እንዲሆን እንዲሰራ እየጣርን የነበረውም ያለነውም። ትግልን እንጂ የሰላማዊ ትግሉን አይደለም እየቀሰቀስን ያለነው አትሳሳቱ። የትግል ምርጫቸውን በግልጽ አስቀምጠው እየታገሉ ያሉት ድርጅቶች የመረጡትን ምርጫ ትክክል መሆኑን እንደሚሰራ በስሜት ሲከራከሩበት በአናይ የትኞቹም ላይ ትክክል አይደላችሁም ምርጫችሁን እንዲሰራ አድርጋችሁ እየሸጣችሁ አይደለም ብለን እንተችበት እንቃወምም ነበር። መረዳታችን የዛን ያህል መሆኑን እወቁልን። እየታገለ ያለው ግቡ ማሸነፍ ስለሆነ ይገባዋል። በተረፈ ዛሬ በአለው የፖለቲካ ትኩሳት ስለምርጫ ማውራት ሰሚ እንደሌለው ይገባነል። አይምሮችን ውስጥ ያለን ሀሳብ ደብቀነው ነገ እንዲህ መሆን ነበረበት ከማለት አውጥተነው ስህተት ብንሆናና ብንተችበት እነመርጣለን። በጎን ምርጫውን ተጠቅሞ ትግሉን ማነሳሳት በምንም መንገድ የትኛውንም ትግል የሚጎዳ መስሎ ቢሰማን ኖሮ ግን ሀሳቡንም አናነሳውም ነበር።

*በተረፈ ምርጫውን አስመልክቶ በእድገታችን በተጫወትናቸው ጨዋቶዎች በሙሉ በየሰፈራችን እፍርታሞች ነበሩ። ለእፍርታሞች መድሀኒቱ ምን እንደሆነ እናውቃለን። ደግሞ ጥርት አድርጎ ማሸነፍ ነው። እፍርታም ድግመህ ስታሸንፈው ነው አፍረው ሽንፈታቸውን የሚቀበሉት። ወያኔን ስናየው ሁለተኛ ሽንፈትን የሚቋቋምበት ምንንም ጀርባ የለውም።*

*Dakotareserch@yahoo.com*
*Date Mar 10 2009*